**ማስጠንቀቅያ/ የመሬት መንቀጥቀጥ**

**እውነታዎች**: በስያትል ውስጥ የመሬት መንቀጥቀጥ ኣጋጥሟል። የደረሰው ጉዳት ምን ያህል መሆኑን ለመገምገም የኣደጋ መከላከያ ሰራተኞች በየቦታው ተሰማርተዋል። የኣደጋ መከላከያ ማእከል በስራ ላይ ነው፡ ከተማይቱም የተቋረጡ ኣገልግሎቶችን እንደገና ለማስጀመር፡ ሰዎችን ከኣደጋ ለማዳንና ለመጠበቅ እየተንቀሳቀሰች ነው።

**ምን ማድረግ ያስፈልጋል**:

- ባሉበት ቦታ ይቆዩ፡ በኣካባቢዎ ያሉትን ሰዎች ተከታተሉ። ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሉ ተንከባከቡ። ወደ ጎዳናዎች፡ ወይም ድልድዮችና ፍሪዌ ኣትውጡ።
- ከመሬት መንቀጥቀጥ በውሃላ ሌሎች ተቀጥያ መንቀጥቀጦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ተጠባበቁ። መሬቱ ሲንቀሳቀስ ሲያዩ ከጠረጴዛ ስር ይግቡ ወይም ጠንከር ያለ የቤት ቁሳቁስ ፈልገው እንደመከላከያ ይጠቀሙበት። ከመስኮቶች ራቁ። ከውጩ ጋር ግንኙነት ከሌለው የማህል-ቤት ግድግዳ ስር ኣጎንብሱ።
- ስልክ ከመደወል ተቆጠቡ። መረጃ ለማግኘት 9-1-1 ኣትደውሉ። ከእጇታቸው የተላቀቁ ስልኮችን ወደ ቦታቸው ይመልሱ። በኣጠቃላይ የስልክ ኣገልግሎት በደዋዮች ተጨናንቋል። የቴክስት መላክ ዕድል ግን ያገኙ ይሆናል።
- ለኣደጋ ግዜ ተብሎ የተቀመጠውን ሁሉ ኣውጡ። ባትሪና የባትሪ ድንጋይ ካሎት ይያዙ። ምናልባት መደበኛ የሙብራት ኣገልግሎት እስኪታገኙ ድረስ ቀናት ሊያልፉ ስለሚችሉ፡ ለሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ራስዎን በራስዎ እየረዱ ለመቆየት ተዘጋጁ።
- የእያንዳንዱ ሰው ደህንነት እንዲጠበቅ በህብረት ስሩ። እርስበርስ ተረዳዱ፡ በኣካባቢ ያሉትን ጎረቤቶች እርዱ።
- ኣደጋውን በሚመለከት ኣዲስ መረጃ እንዳለ ለማወቅ በቀጣይነት ሬድዮ ተከታተሉ ።
- ***ይህንን መልእክት ለመረዳት፡ ለማየትም ሆነ ለመስማት የማይችል የሚያውቁት ሰው ካለ፡ እባክዎትን መልእክቱን ኣስረድዋቸው።***

**ጠቃሚ ዌብሳይቶች**:

http://www.seattle.gov/emergency-management/what-if/hazards/earthquake

http://www.seattle.gov/light/sysstat/

http://mil.wa.gov/emergency-management-division/hazards/earthquake

http://www.ready.gov/earthquakes